# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ፥ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – g l n l m @ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org 2ኛ ደብዳቤ 2005 እ.አ.አ 2nd Quarter 2005


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። (ትንቢተ ኢሳይያስ 54፥13)

# ትንሣዔ

## ተዓምር ወይስ ተረት

የቀደመችው የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ አስተምሕሮ ምን ነበር? የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አስደናቂ ፈጣን ዕድገት ሚስጢሩ ምንድን ነው? በሐዋሪያት ዘመን ወንጌል ዓለምን ለማጥለቀለቅ የቻለበት ጉልበት ወይም ኃይል ከምን የተነሣ ነበር?

የዚህ ሁሉ ጥያቄ መልስ አንድ ነው። እርሱም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣዔ ነው። ሐዋሪያት “ተነሥቷል” የሚለውን የድል መልዕክት ይዘው፡ክርስቶስ ጌታ ሞትን አሸንፎ በአካል መነሣቱን እያስተጋቡ ስለ ዞሩ ነው።

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣዔ የክርስትና ዕምነት ማዕከላዊ ነው። ከሌሎችም ዕምነቶች ሁሉ ልዩ የሚያደርገን ይኸው የጌታችን ሞትን ድል ነሥቶ መነሣት ነው። ስለ ክርስትና ዕምነት ሲነገር ትንሣዔ ከተዘነጋ፦ ክርስትና እንደ ማንኛውም ኃይማኖት ከመቁጠር አይድንም። በእርግጥ በመካከለኛው ምሥራቅ ከፈለቁት በርካታ ኃይማኖቶች ላይ ክርስትና የበላይነትን የተጎናጸፈበት ምክንያት ይኸው የጌታ ትንሣዔ ነው። ስለዚህ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ የጌታን ትንሣዔ መረዳትና ማስረዳት መቻል ግደታው ነው። ይህ መልዕክት ትንሣዔን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሶ ለማመልከት ይሞክራል።

ለመሆኑ፦ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን፡በማያጠራጥር አኳኋን ማረጋገጥ የሚቻለው እንዴት ነው? ይህ ትንሣዔ የተባለ ታላቅ ነገር፡የሆኑ ሰዎች የፈጠራ ወሬ ሳይሆን፡በተጨባጭ ማስረጃ ሊረጋገጥ ይቻል ይሆን?

ይህንን ጥያቄ በተጨባጭ አኳኋን ለመመለስ፡ ትንሣዔ በተወሰነ ታሪካዊ ጊዜና ሥፍራ የተፈጸመ፡ ልበወለድ ሳይሆን ሊረጋገጥ የሚችል ታሪካዊ ዕውነታ መሆኑን ማሳየት መቻል ይጠበቅብናል። ከሐዋሪያት አንዱ “የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሐት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ።” ያለው ለዚህ ነው። (2ጴጥሮስ 1፥16) ጌታ ራሱ በዮሐንስ ወንጌል 2፥18-22 እንደ ተናገረው፡ ትንሣዔ የአምላክነቱ ማስረጃም ስለ ሆነ በቀላሉ ሊወሰድ አይገባም። “… ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት። ኢየሱስም መለሰ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፡በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።” ይህ ብቻ አይደለም። የወንጌላችን የልብ ትርታ ትንሣዔ መሆኑን ታላቁ የወንጌል አርበኛ በመንፈስ ቅዱስ እንደገለጸው እዩ፦ “መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፡ተቀበረም፡ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡ ለኬፋም ታየ፡በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፡ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤…” (1ቆሮ 15፥3-6)

የክርስትናን ዕምነት ማስረጃዎች መርምሬ እንደ ተረዳሁት የጌታ ትንሣዔ ለማመን የማያስቸግር፡ የማስረጃዎቹ ብዛትና ግልጽነት ማንንም ሊያሳምን የሚችል ነው፡

ከማስረጃዎቹ አንዱ (በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፥6) የተጸፈውና ጌታ ከሞት ከተነሣ በኋላ ከአምሥት መቶ ለሚበዙ ሰዎች የታየበት ሁኔታ ከሁሉም የበረታ ነው። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ለሌሎች በርካታ ሰዎች የታየበትና በሐዋሪያት ሥራ 1 ፥ 3 “… ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፡በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።” ተብሎ የተጸፈው ነው። ይባሱንም ደግሞ የዳሰሱት እንጂ እንደነበሩ ሁለቱ ተመልክቷል። “እነሆም ኢየሱስ አገኛቸውና፡ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።” (ማቴ 28፥9) “ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ…አላት።”(ዮሐ ወ/ 20፥17) “… ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፡በእኔ እንደ ምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና፡ እጆቼን ዳሰሳችሁ እዩ አላቸው።”(ሉቃስ 24፥38-39) “ከዚያም በኋላ ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፡ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።” (ዮሐ ወ/ 20፥27)

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች ቢያቀርብም ተጠራጣሪዎች የጌታችንን ሬሳ ተሰርቆ ይሆናል ከማለት አልተቆጠቡም። በሮማውያን፡ በአይሁድ ወይም በደቀ መዛሙርቱ ተሰርቆ ይሆናል ይላሉ።ይሁን እንጂ፡ይህንም አማራጭ እንኳ ብንመረምር፡ተመልሰን ጌታ ከሞት መነሣቱን ለማመን እንገደዳለን፡

እስቲ ተመልከቱ፦ ሮማውያን የጌታን አስከሬን የሚሰርቁበት ምንም ምክንያት አልነበራቸውም። ምክንያቱም እነርሱ ለሚፈልጉት ጸጥታ የማስፈን ተግባራቸው ምንም አይጠቀማቸውም ነበር። የአይሁድ ቀሳውስትም አስከሬኑን መስረቅ አይፈልጉም። የክርስቲያኖች ነገርና መሪያቸው በቶሎ ተቀብሮ እንዲቀር ስለሚፈልጉ ሬሳውን በመስረቅ መከራቸውን ማብዛት አይፈልጉም። ሰርቀውትም እንኳን ቢሆን ኖሮ፡ከሦስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ከሞት ተነሣ ተብሎ ሲገለጽ፡“አስከሬኑን” አውጥተው ለማስተባበያ ባቀረቡት ነበር እንጂ ያን ሁሉ ውርደት ጠጥተው ባልቀሩ፡ ደቀመዛሙርቱም የጌታቸውን አስከሬን ላለመስረቃቸው ግልጽ ነው።እስቲ አስቡት ሞቶ መቀረቱን እያወቁ፡ ያን ሁሉ መከራ ተቀብለው በግፍ ለመገደል ይችሉ ነበር? ለዕውነተኛ ዓላማ የሚሞት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ያ ሁሉ የጌታ የየሱስ ተከታዮች ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት በውሸት ነው ማለት ታላቅ ቅዠት ነው።

የጌታችንን ትንሣዔ ለማካካድ የተደረገው የመጨረሻው የተጠራጣሪዎች መላምት ደግሞ እስውን ቲዎሪ Swoon theory የተባለው ነው። እስውን ቲዎሪ እንደሚለው እየሱስ በመስቀል ላይ ጨርሶ አልሞተም። ነገር ግን (ይላሉ) ነፍሱ እንደ መውጣት ብሎ በኋላ ተመልሶ ነፍስ ዘራ።

ይህ ቲዎሪ ግን ያለልክ የተሳሳተ ነው። እስቲ አስቡት። በውኑ ጌታ እየሱስ ስድስት የፍርድ ምርመራዎችን፡የእሾህ አክሊልን፡ የሮማውያንን ማሰቃየት፡ የመስቀልን ሥቃይ፡በጦር ጎኑን ተወግቶ፡ደሙ ያለልክ ፈስሶ፡ይህም ሳያንስ፦ሦስት ቀንና ሌሊት ያለ ሕክምናና ያለ እሕል ውኃ በሕይወት ቆይቶ፦ በመቃብሩ በር ላይ የተጫነውን ሁለት ሺ ኪሎ ያህል የሚመዝን ድንጋይ ፈንቅሎ በመውጣት፡ በመጨረሻም መሣሪያ ያጥቀው መቃብሩን ይጠብቁ የነበሩትን ብርቱ የሮማ ወታደሮችን ታግሎ ፥ አሸንፎ ማምለጥ ይቻላል? በፍጹም አይሆንም። ስለዚህ “እስውን ቲዎሪ” ከቅዠትነት አልፎ ሊታሰብ አይችልም።

ስለዚህ የጌታ እየሱስን ትንሣዔ በጥንቃቄ የመረመረ ሰው ሁሉ የሚደርስበት ድምዳሜ፦ በእርግጥ ሞትን ድል ነሥቶ በመነሣት ጌታና አዳኛችን ሆኖ፡ በሕይወት እንዳለ ነው። “ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ፡ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፦ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ፤ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። (ዮሐ/ራዕይ 1፥17-18)

በመጨረሻም የጌታችን ትንሣዔ መታሰብ ያለበት በስቅለት በዓል ሰሞን ብቻ አለመሆኑን ማሳሰብ አለብን። ይልቁንም በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንዲሞላን በየዕለቱ መታሰብ አለበት። ምክንያቱም የየሱስ ትንሣዔ፡ ፈሪና ተጠራጣሪ የነበሩትን ሐዋሪያት ወደ ጀግኖች ታሪክ ሠሪነት የለወጠ ብቻ ሳይሆን፦ ዛሬም የብዙዎቻችንን ሕይወት እየለወጠ ስለ ሆነ ነው በእርሱ መኖር ምክንያት እኛም በሕይወት እንኖራለን። በመጨረሻም መጽሐፍ እንደሚል፦ በቅጽበተ ዓይን በእርሱው አምሳል ወደ ትንሣዔ አካል ተለውጠን ወደ ዘላለም ክብሩ እንገባለን፡አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን።

# ድምፁን መስማት

እጅግ ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለማድረግ እየተቸገርህ ነህ? ምን ዓይነት ሥራ ልምረጥ፥በየትኛው ከተማ ልኑር፥ በየትኛው ቤተ ክርስቲያን ሆኜ ላምልክ ወይም የትኛዪቱን ሴት ላግባ፥ ወዘተ በሚለው ሐሳብ ላይ መወሰን ቸግሮሃል? ምናልባት ያለህበትን ሐገር ሆነ ወዳጆችህን ተለይተህ ስለ መሄድ መወሰን ተስኖህ የጌታን ምሪት ትለምን ይሆናል።አለዚያም፦ ከወዳጅ ዘመድ ጋር በገጠመህ ችግር ምን ማድረግ እንዳለብህ ጠፍቶህ ለምሪት ትጸልይ ይሆናል።

በዚህ ዓለም ስንኖር በየዕለቱ የተለያዩ አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንገደዳለን። ከዚህም ማምለጥ አይቻልም።

ይህን ጽሑፍ በምታነብበት ጊዜ አስቸጋሪ ውሳኔ በማድረግ ላይ ትሆን ይሆናል:: ባትሆንም እንኳ ወደፊት ውሳኔ የሚጠይቅ መንታ መንገድ ያጋጥመሃል:: ይህም ሊያስገርም የማይገባ የሕይወት ዕውነታ ነው::

እንዲህ በሕይወት መንታ መንገድ ላይ ስንደርስና  ወደ ግራ ወይም  ወደ ቀኝ÷ የትኛውን መምረጥ እንደሚሻል ግራ ሲገባን ሁላችንም የሚያስፈልገን አንድ ነገር ነው:: እርሱም:- ትክክለኛውን ውሳኔ ለማድረግ  የሚያስችል  የእግዚአብሔር ምሪት (ድምፅ) ነው::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን÷የሰብአዊነታችን ውስንነት በገሃድ ይታወቀናል:: ስለዚህም  እግዚአብሔር አምላክ በማያጠራጥር  ጉልሕ ድምፅ ምሪቱን እንዲያሰማን በትጋት እንጸልያለን:: እንጠባበቀውማለን:: ምናልባት÷በቃሉ ውስጥ ቢናገረኝ በማለት መጽሐፍ ቅዱሳችንን እናገላብጣለን:: ቅዱሳንን እናማክራለን ወዘተ÷ ጥበቃው እየተራዘመ ሲሄድም÷የእግዚአብሔርን ድምፅ መናፈቃችን እየጨመረ ይሄዳል:: ጌታ ሆይ ምነው ራቅህ? ፊትህንስ ለምን ሰወርህ?  በእኔ በባሪያህ ስለ ምን ጨከንህ? ማለት እንጀምራለን::

ወዳጄ ሆይ:-እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ራስህን ብታገኝ÷ ይህ በአንተ ብቻ የሚሆን መስሎህ አትደነቅ:: የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት÷አንዳንድ ጊዜ ለምን እንዲህ  እንደሚያስቸግር  ብዙዎቻችን ተገርመናል::  ጌታ ግን ድምፁን ለመስማት ያለን ጉጉት ፍጹም ሆኖ ሲያገኘን፡ ከአሁን ቀደም  ያልለመድነውን  ጥልቅ ዕውነቱን ይገልጽልናል::  ይኸውም ለትንሿ ጥያቄያችን መልስ ከመስጠት አልፎ÷<u>ራሱን ለእኛ መግለጽ ነው</u>÷ክብር ለስሙ ይሁን::

ሙሴ አርባ ዓመታት በበረሃ ውስጥ ካሳለፈ በኋላ  ተስፋ  መቁረጥ ÷ ድካምና ጥርጣሬ ሳይጀምረው እንደማይቀር እገምታለሁ:: ሆኖም:- <u>ከራሱ የሆነ መመኪያ ምንም ባልቀረለት ደረጃ ላይ አድርሶት ጌታ ሊገናኘው እንደ ፈለገ እንረዳለን::</u>

በኦሪት ዘጸአት 3÷1-6 መሠረት የሚከተሉትን አምስት አበይት ሐቆች ማስፈር እንችላለን::

**1ኛ. <u>በማንኛውም ወቅት የምናልፍበትን ማንኛውንም ሁኔታ ጌታ እግዚአብሔር ያውቃል::</u>**

መጽሐፍ የሚለውን ተመልከቱ:- “ሙሴም  የዮቶርን  የአማቱን  የምድያምን ካሕን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ ወደ  ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ ÷ ወደ  እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ::”

(ዘጸአት 3÷1)

አስቲ ይህንን ቃል  ልብ  እናድርግ:- የአማቱ በጎች እረኛ የነበረው ሙሴ÷በጎቹን ወደ በረሐወማው÷ወደ ምዕራብ ነዳ በዚያንም ጊዜ ኮሬብ ወደ ተባለው የእግዚአብሔር ተራራ መጣ::  <u>*በዕውነቱ ሙሴ ወደ ኮሬብ በጎቹን የነዳው በአጋጣሚ ነበር?*</u> አይደለም::  ሁሉን የሚያውቀው ጌታ እግዚአብሔር:- ሙሴ በዚያን ጊዜ አምላኩን ለመገናኘትና ፈቃዱን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ መሆኑን ስለሚያውቅ ወደዚያ መርቶት ነው::

የአንተንም ሁኔታ እግዚአብሔር አምላክህ በሚገባ ያውቃል:-  ክብር  ለስሙ ይሁን:: ድምፁን ለመስማትና ሳታቅማማ ለመታዘዝ መቼ ዝግጁ እንደምትሆን በትክክል ያውቃል:: ስለዚህ ጸሎትህን ቀጥል::  ጌታ ስለማይዘገይ ÷ በትዕግሥት ተጠባበቅ::

**2ኛ. <u>እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር የጠበቀ ወዳጅነትን ይሻል::</u>**

“የእግዚአብሔርም መልአክ  በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው፤እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ::”

(ዘጸአት 3÷2)

ሙሴ:- ወደ ኮሬብ በደረሰ ጊዜ ሁለት ነገሮችን አየ:: እነርሱም የእግዚአብሔር መልአክና የሚነድድ÷ነገር ግን የማይቃጠል ቍጥቋጦ ናቸው:: እነርሱም ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘቱን ሊያረጋግጡለት በቂ ነበሩ÷ጌታ የባረከ::

አንተንም:-  እግዚአብሔር አምላክህ በማትጠራጠርበት አኳኋን  ሊገለጥልህና ታዝዘህ እስክትከተለው ድረስ  ሊናገርህ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል:ክብር ለስሙ ይሁን::  በሚመች ወይም በማይመች ሁኔታ ውስጥ በማሳለፍ ወደ እርሱ እንድታተኩር ካደረገ በኋላ÷ከዚህ በፊት አይተኸው በማታውቀው ሁኔታው ራሱን ይገልጽልሃል÷ይከብርብህማል:: ያከብርህማል::

**3ኛ. <u>ጌታ  ወደ  እርሱ  እንድንመለከት ይጋብዘናል::</u>**

ሙሴ የሚነድደውን ቍጥቋጦ ባየ ጊዜ ምን ሆነ? “ሙሴም:- ልሂድና ቍጥቋጠው ስለ ምን አልተቃጠለም÷ይህን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ::” (ዘጸአት 3÷3)

ከዚያም አስገራሚውን እሳት ተመልክቶና አድንቆ:-  የተለመደውን  የእረኝነት ሥራውን መቀጠል ይችል ነበር:: ሙሴ ግን÷ጊዜ ወስዶ ÷ ምን ይሆን?  በማለት ለመረዳት ቀረበ::

ወገኖች:-የእግዚአብሔርን ነገር÷ምን ይሆን ብሎ÷ ቀርቦ  መመራመር  እንደ ሙሴ ላሉ ጥቂቶች በተለይ የተሰጠ አይደለም:: ቢሆንማ ኖሮ:-ጌታ ራሱ“<u>ለምኑ ይሰጠችሁማል ፡ ፈልጉ  ታገኙማላችሁ፡ መዝጊያን አንኳኩ÷ይከፈትላችሁማል::</u>” ብሎ ባልመከረን ነበር:: (ማቴዎስ 7÷7) ስለዚህ:- በሽንፈት÷ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ÷ ወይም አስገራሚ ሁኔታ ሲያጋጥምህ:-ጌታ ፊቱን እንዲገልጽልህ ፈልግ:: ከቃሉ ውስጥ እንቆቅልሽህን ወደ ምትፈታበት  የመጽሐፍ  ቅዱስ  ክፍል እንዲመራህ ለምነው::

**4ኛ. <u>እግዚአብሔር የሚናገረው÷ ለመስማት ስንዘጋጅ ነው::</u>**

ሙሴ በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ መደነቁንና ለማየት መቅረቡን ባየ ጊዜ÷ጌታ በስሙ ሲጠራው ተመልከቱ:: “እግዚአብሔር እርሱ (ሙሴ) ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ ...ከቍጥቋጠው ውስጥ እርሱን ጠርቶ:- ሙሴ÷ሙሴ ሆይ አለ::” (ዘጸአት 3÷4)

ወገኔ:- በዚህ ዓለም መሻትና በኃላፊነቱ ላይ በማተኮር÷የእግዚአብሔርን ነገር አተኵረህ ለማየት ተስኖህ ይሆን? ከሆነ በንስሐ በፊቱ ቀርበህ÷በአንተና በሕይወትህ ዓላማ መካከል÷ ግርዶሽ ሆነው የቆሙትን ነገሮች እንዲያስወግድልህ ጸልይ ከዚያም የማያሳስተውን ድምጹንና ምሪቱን ማስተዋል ትጀምራለህ፤ ክብር ለስሙ ይሁን::

**5ኛ. <u>እግዚአብሔር ራሱን ይገልጽልሃል፤ አንተም ታስተውላለህ::</u>**

ሙሴ በተጠራ ጊዜ <u>እነሆኝ</u> አለ::ከመጀመሪያውም ጌታ ከሙሴ ይጠብቅ የነበረው ይኸው ነበር::  ችሎታውና ሥልጣኑማ ምንጊዜም ከጌታ ነው::  ስለዚህ ሙሴ ተዘጋጅቶአልና ከአገልግሎት ሆነ ከማምለክ÷መቅደም ያለበት ዋናው ነገር እንዲህ ተብሎ ተነገረው:: “ወደዚህ አትቅረብ፤<u>አንተ የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች ናትና÷ጫማህን ከእግርህ አውጣ</u> አለው::” (ዘጸአት 3÷5)

ይህ  በዕውነት  ከእግዚአብሔር  ጋር የተገናኘ ሰው የሚታወቅበት÷ የቅዱሳን ምልክት ነው:: እንዲህም ላሉት ጫማቸውን ያወለቁ (ትሑታን) ቅዱሳን ÷ ጌታ ራሱን መግለጽና ማስተዋወቅ ደስ ይለዋል ፤ ስሙ ይክበር:: ሙሴ  በሙሉ  ልቡ ወደ ጌታ ለማተኮር በተዘጋጀ ጊዜ ጌታ ለመናገር መፍጠኑን ተመልከቱ:-  “እኔ የአባትህ አምላክ÷ የአብርሃም አምላክ÷ የይስሐቅም አምላክ:የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው::” (ዘጸአት 3÷6) ከዚህም ቀጥሎ ሙሴ ስለ ጌታ ክብር  ፊቱን  ሲሸፍንና ጌታም የወደፊት አገልግሎቱን ዝርዝር መግለጫ ለተዘጋጀው ባሪያው ሲገልጥለት እናነባለን÷እግዚአብሔር ይመስገን::

እንግዲህ ወዳጅ ሆይ:- እግዚአብሔር ሲናገር ካልሰማነው  መልካም ስለማይሆን:-ከመናገሩ አስቀድሞ÷ ለመስማት መዘጋጀታችንን ማረጋገጥ አለበት::  እንደ ሙሴ አርባ ዓመታት  ቢፈጅም እንኳን ይጠብቃል እንጂ:- ለመስማት ሳልተዘጋጀ ሰው አይናገርም:: ድምፁን ተጠምቶ በሙሉ ትኵረት ለተዘጋጀ ሰው ግን ጌታ ለሙሴ እንዳደረገው÷ባሕሪውንና ቅድስናውን ፈቃዱንም ለመግለጥ አይዘገይም ክብር ለስሙ ይሁን::

በጥሞና ጸሎት÷ ጊዜ ወስዶ÷ እግዚአብሔርን ማዳመጥና መስማት  ማንኛውም ክርስቲያን በምድራዊ ዘመኑ መለማመድ  ካለበት ሁሉ ይልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው::  የጥሞና ጊዜ በጌታ ነገር ላይ በጸሎት መንፈስ  ሆኖ ማሰላሰል (meditate) ማለት ነው::  በጌታ ፊት የግልን ቃላት ሳያበዙ÷ልብንና አዕምሮን ሁሉ በጌታ ላይ  በማተኮር ÷ ስለ እርሱ ማሰላሰልና  እርሱ ለልባችን እንዲናገር ምቹ መሆን ነው::

ራስን በዚህ መልክ ማጎልመስ ወደ ሦስት  ተፈላጊ  ክርስቲያናዊ  ደረጃዎች ያደርሳል::

**1ኛ. <u>ቅድስና:-</u>**

ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት በጸሎትና በጥሞና  የምንሆንበት  ጊዜ  ሳይኖረን÷ በታዛዥነትና በቅድስና  ለመኖር ማሰብ “የሕልም እንጀራ”  ከተባለው ምሳሌ አያልፍም::ይህም ማለት÷አንድ ቀን ጸሎት ብናስተጓጉል ቅድስናችንን እናጣለን ማለት አይደለም::  ነገር ግን  ዕውነተኛ ቅድስና የእግዚአብሔርን ነገር በመጠማት በሚቀጣጠል የዘወትር ሕይወት የሚገነባ እንጂ÷በፍርሃት የሚደረግ የኃይማኖት መልክ አለመሆኑን ለማሳየት ነው:: እንዲሁም ሳምንቱን ሙሉ የሥጋን ፍላጎት በማርካት ሰንብተን÷ ዕሑድ ድምፁን ለመስማት  ቢሳነን  ልንገረም አንችልም:: ዳሩ ግን ወደ ፊቱ ዘወትር መቅረብ ናፍቆትህ ሲሆንና÷ ሲናገርህም  ሰምተህ መታዘዝን ስትለምድ÷ረቂቅ ጥበብንና የጌታን ባሕሪያት ትገነዘባለህ::  ስለሆነም ክርስቲያን ሆኖ ይህን ኣለመፈለግ ራስን ከመበደል በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም::

**2ኛ. <u>የርካታ ሕይወት:-</u>**

ያለ ቅድስና  የመንፈስ ርካታ አይገኝም:: ስለዚህም በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ማንነት በማወቅ ጥማት ውስጥ ሳንገባና እርሱንም መጠማት ሳንለምድ÷ዕውነተኛ  የሕይወት ስኪትና  ርካታ ፈጽሞ አናገኝም::

**3ኛ. <u>ሰዎችን  የመርዳት  አገልግሎት:-</u>**

እንደ ሙሴ ችሎታና የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ያላቸው እንኳን ቢኖሩ:- በራሱ

ችሎታ እግዚአብሔርን ማስከበር የቻለ፡ ማንም ታይቶ አያውቅም፡፡ ሙሴም ቢሆን ሕዝበ እስራኤልን ወደ ነፃነቱ መምራቱ በጠራውና ባስቻለው በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ልጅ ትምሕርትና ችሎታ ያደረገው ምንም አልነበረም፡፡ ስለዚህ፦ እግዚአብሔርን ለማወቅ ጊዜአችንና ልባችንን ስንሰጥ፥ ሕይወታችንን እርሱ እንዲቆጣጠር እንስጠዋለን ማለት ነው፡፡ ከዚያም በእርሱ በራሱ ሥልጣንና አሠራር፥ ፍቅሩንና ማጽናናቱን ወደ ሌሎች ወስደን እናገለግላቸዋለን፡፡

በመጨረሻም፦ እግዚአብሔርን መጠባበቅና እርሱንም በመስማት ውስጥ መኖር አንድ ነገርን ግድ ይላል፡፡ እርሱም "እነሆኝ" በማለት ወደ እርሱ የሚጮኽና ጌታ የተናገረውን ማንኛውንም ቃል ለመታዘዝ የቆረጠ ልብ ነው፡፡ እንዲህም ያለ ልብ እግዚአብሔርን የማወቅ ጥማቱ ይረካል፤ፈቃዱንም የመፈለግ ርሐቡን ይጠግባል፡፡ ከዚያም ውሳኔ ማድረግ ሲመጣ፥በድንግዝግዝ መጭበርበር አይኖርም፡፡ በእግዚአብሔርም ፊት ባልተረጋገጠ ሕይወት አንመላለስም፡፡ ግራ በተጋባ ሕይወት ፈንታ፥ በአባቱ ቤት በብርሃን ውስጥ እንደሚኖር በአባቱም ፈቃድ ዕውቀትና ደስታ ውስጥ እንደሚኖር ልጅ የተባረከ ፍሬያማ ሕይወት እንኖራለን፡፡ ጌታ ስሙ ለዘላለም ይክበር፡፡

## መቅበሪያን ለመሻገሪያ

አንድ ገበሬ ነበረ። እርሱም ላሞች፣ በጎችና አህዮች እንዲሁም ሌሎች እንስሶች ነበሩት። ከዕለታት አንድ ቀን እንስሶቹ ሁሉ ከዋሉበት ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ አንዱ አህያ ላለወትሮው ሳይመለስ አመሸ።

ገበሬውም በነገሩ ተደናግጦ አህያውን ሲፈልግና ሲያስፈልግ አድሮ ነጋበት። በነጋታውም እንዲያፋልጉት ጎሮቤቶቹን ለምኖ፣ ሲፈልጉ ከዋሉ በኋላ፦ አህያውን በአንድ ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ አገኙት።

ሕዝቡም ሁሉ ተባብረው አህያውን ከወደቀበት ጉድጓድ ለማውጣት የሚችሉትን ሙከራ አደረጉ። ሆኖም አልቻሉም። በመጨረሻም የአህያው ባለቤት፣ የሕዝቡንና የአህያውን መዳከም አይቶ "ተውት፥ተስፋ የለውም፥በዚያው ባለበት፥ አፈር እናልብሰውና እንገላገል" ሲል እያዘነ ሕዝቡን አዘዘ። ሕዝቡም ጉዳዩ አታክቶአቸው ስለ ነበረ በሃሳቡ ተስማሙ።

በዚህን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው አካፋውን አመጣና፥አፈር እየዛቁ፥ይሞት ዘንድ በአህያው ላይ መድፈን ጀመሩ። አህያው ግን የሚያስገርም ነገር ያደርግ ጀመረ። አፈር እየተዛቀ በላዩ በተከመረ መጠን አካላቱን በኃይል በመነቅነቅ አፈሩን ያራግፍ ጀመር። የተጫነውን የአፈር ክምር ከላዩ ካረገፈ በኋላም ከፍ በማለት በላዩ ይቆም ጀመር። ሕዝቡ ሊቀብሩት የሚያፈስሱበትን አፈር እያራገፈና እየተረማመደበት ቀጠለ።ጉድጓዱ እየሞላ አህያውን ወደ ላይ እያቀረበ ሄደ። በመጨረሻም ተዓምረኛው አህያ፥ለመቃብሩ በታሰበው የአፈር ክምር ላይ ተረማምዶ ሃ! ሃ! ሃ! እያለ ከጉድጓዱ ወጣ። በደስታም ጌታውን እያሸተተ ተከትሎት ወደ ቤቱ አመራ።ሊቀብሩት የነበሩት ሕዝብም ሙሽራ ያጀቡ ይመስል ፥ በዘፈን አጅበውት ነበር። ገበሬውና ሕዝቡም ደስ አላቸው።

ተስፋ በሚያስቆርጥ፥ ጉድጓድ በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ያለ ሰው አለ። የእኔስ ነገር፥ ተስፋ የለውም፤ ከዚህስ የሚያወጣኝ ምን መላ ይገኛል? የሚል ሰው አለ። "በወደቀ ዛፍ ላይ መጥረቢያ" እንደሚበዛ፦የሚሆነው ሁሉ ሊቀብረው የሚደራረብበት ይመስለዋል።

ነገር ግን ከዚህ አህያ ታሪክ እንደምንማረው፥ሊቀብረው የሚወድቅበትን ጫና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፥ በዕምነት ማራገፍ ይቻላል። በዕምነትም ቀና ብሎ በላዩ መቆምና በምሥጋና ወደ ላይ መውጣት ይቻላል። ጌታን በማመስገን በችግራችን ላይ የነበረውን ትኩረታችንን ወደ ላይ፥ወደ ፀባዖት ከፍ ስናደርግ፥ሊቀብረን የነበረው ጫና ራሱ መረማመጃና መውጫ ሲሆነን እንመለከታለን፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

ወገኔ፥ ሊቀብርህ የሚጫንህን ክፉ ነገር በእግዚአብሔር ታምነህ በፊቱ አራግፈው ከዚያም በዕምነት ቀና ብለህ ተረማመድበት፤ ጌታም በድል ያሻግረሃል። ልቅሶህም ወደ መዝሙር ትካዜህም ወደ ሐሴት ይለወጣል።ይህም የአምላክህ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው።"ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።" ጌታ ስሙ ይክበር። (የማርቆስ ወንጌል 9፥23)

## የንጉሥ ጉብኝት



በእንግሊዝ ሐገር ራቅ ባለው ባላገር ትኖር የነበረች አንዲት ወጣት ገበሬ ነበረች ይባላል፡፡ እርስዋም በአንድ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የምትኖር ቆንጆዬና ንቁ ልጃገረድ ስትሆን ስሟም ኢገርሐርት ይባል ነበረ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን የእንግሊዙ ንጉሥ ያቺን የገጠር መንደር የሚጎበኝ መሆኑ ተነገረ፡፡ ይህም ማለት እንደ ንጉሡ ልማድ፥ ከመንደሩ መኖሪያዎች ማንኛውንም ቤት በድንገት ሊጎበኝ ይችላል ማለት ነበር፡፡

ኢገርሐርት፥ንጉሡ ወደ መንደሯ መምጣት እጅግ ስላጓጓት ወዲያው ዝግጅት ጀመረች፡፡ ጎጆዋን አጸዳዳች፡፡ መጋረጃዎቿን አጥባ ተኰሰች፡፡ ሁሉንም ነገር ንጹሕና መልካም ሽታ ያለው አድርጋ አሰናዳች፡፡

ዝግጅቷንም እንደ ፈጸመች ምናልባት ንጉሡን ሳታይ እንዳያመልጣት ወደ መሐል መንደር ለመውጣት ትቸኵል ነበር፡፡ ነገር ግን ልክ ልትወጣ ስትል፥በድንገት በሯ ተንኳኳ፡፡ እርስዋም "ንጉሡን እንዳላይ ሊያስተጓጉለኝ፥ የመጣብኝ ማን ነው?"እያለች በሯን ከፈት ስታደርግ፡ ራሷን በሻሽ የሸፈነችና ሕፃን ልጅ የታቀፈች አንዲት የገበሬ ሚስት መሳይ ሴት ቆማ ነበር፡፡ ሴትየዋም፥"እባክሽን የኔ እመቤት፡- ረዥም መንገድ ስጓዝ ውዬ፡- ደክሞኛልና፥ እቤትሽ ገብቼ ውኃ እንድ ጠጣና እንዳርፍ ፍቀጂልኝ" ስትል ለመነቻት፡፡

ኢገርሐርትም፥"ግቢና ዕረፊ፤ ውኃም ጠጪ፡፡ እኔ ግን መቆየት አልችልም፡፡ ንጉሥ ወደ መንደራችን ሊመጣ ስለ ሆነ ሳላየው እንዳያመልጠኝ ወደ መንደር መሮጥ አለብኝ ፡፡ ቶሎ እመለሳለሁ፡" ብላ ወጥታ በፍጥነት ሄደች፡፡

እየገሠገሠችም ከመንደሩ መግቢያ ስትደርስ ከሦስት ስጦታ መሳይ ነገር የተሸከሙ ሰዎች ጋር ተገናኘች፡፡ እነርሱም ወደ መንደሯ የሚወስደውን መንገድ ጠየቋት፡፡ እርሷም ነገረቻቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሐብታም የምሥራቅ ሐገር መንገደኞች ወደ መንደሯ ማምራታቸው ገረማት፡፡

ከሦስቱ መንገደኞች አንዱም መገረሟን ተረዳና፦ "እኛ የሩቅ ሐገር ሰዎች ነን፡፡ ንጉሥ ወደዚህ መንደር እንደሚመጣ ተረድተን መምጣታችን ነው" አላት፡፡ ኢገርሐርትም፦ "ዕውነት ነው፡፡ እኔም ወደ መንደሩ የምሄደው ለዚሁ ነው" አለቻቸው፡፡ እነርሱ ግን፦ "እኛ እንደምናውቀው ግን ንጉሡ የሚመጣው ከከተማ ውጭ፥ በገጠሩ ነው"፡ አሉአት፡፡

እርስዋም ሳትከራከር በእንግዳ አነጋገራቸው ተገርማ መንገዷን ቀጠለች፡፡ ከመንደርም ደረሰች፡፡ ወዲያውም ብዙ መንደርተኞች ወደ ገጠሩ ሲጎርፉ ተመለከተችና በመገረም፦ "ወዴት ነው የምትሄዱት" ስትል ጠየቀቻቸው፡፡ አንዱም ሲመልስላት፦ "ይመጣል የተባለው ንጉሡ፥መጥቶ፡ በገጠሩ ውስጥ ገብቶአል ስለተባለ ወደዚያ እየቸኮልን ነው" አላት፡፡

ኢገርሐርትም በከንቱ በመድከሟ እየተጸጸተች ሕዝቡን ተከትላ ተመለሰች፡፡ ከሁሉ የባሰው ደግሞ የሕዝቡ ጉዞ በቀጥታ ወደ ጎጆዋ ማምራቱ ነው፡፡ ቤቷም ደርሳ፥ ጎጆዋ በሕዝብ ተከቦ ስታገኝ፥ "ይህስ አይሆንም፦ ያችማ ጎጆዬ ናት፡፡ ንጉሡ በዚያች ሊሆን አይችልም"፡እያለች በሯን ከፍታ ገባች፡፡ ያቺው ራስዋን በሻሽ ተሸፍና፥ ልጅ ታቅፋ የነበረችዋ፥ ገበሬ የመሰለች ሴትዮ ቤት ውስጥ ትታት እንደ ሄደችው ጠበቀቻት፡፡

በዚህን ጊዜ፦ እንግዳዪቱ ብድግ ብላ ቆመችና፥ሻሽዋን ከራስዋ ላይ አወረደች ኢገርሐርትም አወቀቻትና፥ትንፋሽ እስኪያጥራት ድረስ በድንጋጤ ተዋጠች፡፡ ወዲያውም በግምባርዋም ተደፍታ እጅ ነሣች፡፡ "ምን ነው፥ምን ነው ቆይቼ በነበር? ያን ሁሉ በመንገድ ያጠፋሁትን ጊዜ ከንጉሡ ጋር ባሳለፍሁ ነበር፡፡ ምን ነው አስተውዬ በነበር? እያለች ጸጸትዋን ገለጸች፡፡ ምክንያቱም የገበሬ ሚስት መስላ የመጣችው እንግዳ የእንግሊዟ ንግሥት፡ ስትሆን ሕፃኑም ልዑል አልጋ ወራሹ ነበር፡፡ ወጣቷም ገበሬ፥ ምንም እንኳን በቂ ዝግጅት አድርጋ የጠበቀች ብትሆንም፥ ከንጉሡ ጋር በመተላለፍ ጊዜዋን በከንቱ በመሯሯጥ ስላባከነች ተቆጨች፡ ይባላል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ፥እንደ ኢገርሐርት፦ ንጉሡ መሲሕ እንደሚወለድ ያውቁና ይጠባበቁ የነበሩ ብዙ ነበሩ፡፡ ሆኖም በቤተ መንግሥት እንጂ በከብት በረት ውስጥ አልጠበቁትም ነበር፡፡ ስለዚህም ብዙዎቹ አላወቁትም፡፡ "የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፤ለተቀበሉት ግን በስሙም ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡"(ዮሐ/ወ 1፥12)

ዛሬም ኢየሱስን ለሚቀበል የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ይሰጠዋል፡፡ የዘለዓለሙ ንጉሥ ይታደግ ዘንድ ዛሬም ወደ ብዙዎች ይመጣል፡፡ ያላወቁት እንዲያውቁት፥ያወቁት ደግሞ በፍቅሩ እንዲረኩ ይጎበኛቸዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ያላወቁት ይስቱታል፤ያወቁት ደግሞ ሲሯሯጡ ይተላለፉታል፡፡ይህ ጽሑፍ ራሱ የንጉሡ ጉብኝት ነው፡፡ ለሚቀበል መዳን ይሆንለታል፡፡

ወገኔ ሆይ፦ አንተስ እንዴት ነህ? ንጉሡን ኢየሱስን አውቀኸዋል? ስለ መምጣቱስ ተረድተሃል? ቤትህን አሰናድተህ፥ ልብስህን አንጽተህ፥ ልትቀበለው እየተጠባበቅህ ነህ? መልስህ አዎንታ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ንጉሡ ለፍርድ የሚመጣበት ጊዜ እጅግ በቀረበበት በዚህ ጊዜ እርሱን ቸል የማይል ሰው ብሩክ ነው፡፡

የንጉሡ ወዳጆች እርሱን በማክበር፥ያላወቁት ደግሞ እርሱን ለማወቅ መትጋት

የሚገባበት ወሳኝ ዘመን ላይ ተደርሷል:: <u>መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ</u> የሚለው ጥሪ በግልጽ ለሁሉ እየቀረበ ነው:: ይህም የዘመን መፈጸም ምልክት ነው:: ስለዚህ ንጉሡን እየሱስን ለመቀበልም ሆነ ለማምለክ ችላ ማለት የዘላለም ጸጸት ሊሆን ዘመኑ እየቸኮለ ነው:: ስለዚህ አንተ የምትተኛ ንቃ:: እግዚአብሔርም ያበራልሃል::

## ለዳግማዊ ልደት የንሰሐ ፀሎት:-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ:- ኢየሱስ ስለ ኃጢአቴ መሞቱን አምናለሁ:: ጌታዬና አዳኜ መሆኑን እቀበላለሁ:: ከዛሬ ጀምሮ አንተን በመፍራት እኖራለሁ:: ኃጢአቴን ይቅር በለኝ:: ሥርዓትህን አስተምረኝ:: ስለ ሰማኸኝና ስለ ተቀበልኸኝ ተመስገን:: አሜን::

## ትሠግሮቻችን

እጅግ የወደድኋችሁ የጌታ ቤተሰቦች የ"ከእግዚአብሔር ፍቅር" አዘጋጆች :- የእግዚአብሔር በጎነት ዘወትር እንዲበዛላችሁ የሁልጊዜ ፀሎቴ ነው:: የመስቀሉ ፍቅር ግድ ብሏችሁ ÷ መንግሥቱን ለማስፋት ስለምታደርጉት አገልግሎት ጌታ ይባርካችሁ፣ቅናታችሁንና ለነፍሳት ያላችሁን ጥልቅ ፍቅር በመልዕክታችሁ አስተውላለሁ:: ከመታወቅም በላይ የሆነውን ጌታ እንደገባችሁና በደረሳችሁበት ስለምታገለግሉት:- ለስሙ ያደረጋችሁትን ይረሳ ዘንድ የእኔ ጌታ አመጸኛ አይደለም::

ሌላው:-ጽሑፎቻችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ÷ ለማንም ጥያቄ የማይፈጥሩ ንፁሕና ለመረዳት የሚመቹ መሆናቸው ነው:: ላልዳኑት ብቻ ሳይሆን የዳኑትንም የሚያነቃቃና የሚያበረታታ አገልግሎት በመሆኑ እጥፍ ጠቃሚ ነው አብዛኛው ሰው ግራ ተጋብቶ የየራሱን ኑሮ ዕቅድ በሚያወጣበት በዚህ ዘመን:- እውነትም ከእግዚአብሔር ፍቅር በሆነችው ደብዳቤአችሁ÷ አማኞችን ለማጽናናትና የጠፉትን ለመመለስ በምታደርጉት ትጋት ጌታ መንፈስ ቅዱስ በኃይልና በጸጋ እንዲያበረታችሁ ፀሎቴ ነው::

በመልዕክቶቻችሁ ብዙ ተጠቅሜ አለሁ:: የሚገርመው ደግሞ በብዛት ካለሁበት ሁኔታ ጋር ስለሚጋጠም የሚያንፅ ትኩስ የእግዚአብሔር ድምፅ ሆኖልኛል::ስለዚህ የምትልኩልኝን መልክት ካነበብሁ በኋላ:- ለሌሎች አስተላልፋለሁ:: አምላኬ እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ እየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል:: አሜን::

ማርታ ወንድይራድ
አቡዳቢ
ዩናይትድ አረብ ኤመረት

እህታችን ማርታ:- የምናገለግለው ጌታ እየሱስ ያስብሽ:: ሌሎችን በምናጽናናበት መጠን እኛም መጽናናት እንደሚያሻን ስላሰብሽን ጌታችን የእስራኤል ቅዱስ ከማደሪያው ያስብሽ:: ስለ ላክሽልን የፖስታ ቴምቤሮች በጣም እና መሰግናለን:: ጌታ አብዝቶ ይባርክሽ::

ከእግዚአብሔር ፍቅር

# የእየሱስ ስም ሞገዱን ሲያዝዝ

ናቫልዲ:- ስሪላንካ (ቀድሞ ሲሎን ይባል የነበረ ደሴት)





ዳያላን ሳንደርስ የተባለ የስሪላንካ ተወላጅ የአሜሪካን ዜጋና ነዋሪ ነበር:: ይህ የጌታ እየሱስ ተከታይ የሆነ ሰው በትውልድ ሐገሩ በጎሣ ጦርነት ምክንያት ወላጅ አልባ ለሆኑት ሕፃናት ወገኖቹ ሸክም ስለ ተሰማው÷ በአሜሪካን የነበረውን ቤቱን ሸጦ÷ ወደ ሐገሩ ተመለሰ:: ከዚያም ናቫላዲ በተባለች አነስተኛ የዓሣ አጥማጆች መንደር÷በ1994 ዓም እአአ 'ሳምራዊያን መዋእለ ሕፃናት' የተባለ ድርጅትን መሠረተ::

ወንድማችን ሳንደርስ (ራሱ እንደ ተናገረው) ታሕሣስ 29÷2004 ጧት ማልዶ በነቃ ጊዜ÷የነበረውን ሁኔታ ሲገልጽ:- "እጅግ ጸጥ ያለ ንጋት" ነበር:: "ከጸጥታውም የተነሣ÷የባሕሩ ወለል የተነጠፈ መስተዋት ይመስል ነበር"ብሏል:: እርሱም በዚያን ቀን የሚሰብከውን መልክት ያሰላስል ነበር:: እርሱ ካለበት ጥቂት ራቅ ብሎ ደግሞ ሃያ ስምንት ሕፃናት ወደ ፀሎት ለመሄድ ይሰናዱ ነበር:: ይህ በእንዲህ እንዳለ ነበር በኃይል የሚሮጥ ሰው መሳይ ድምፅ ለሳንደርስ የተሰማው:: ወዲያውም ያለልክ የተደናገጠች ባለቤቱ በሩን በርግዳ ገባች:: እርሷም "ባሕሩ÷ባሕሩ እየመጣ ነው:: ና! ውጣ! ባሕሩን እየው::" እያለች ወተወተችው::

ወዲያውም ሳንደርስ÷ባለቤቱ ኰሂላ ያለ ልክ መደናገጧን አይቶ÷ "ረጋ በዪ:: እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው:: ያለ እርሱ ፈቃድ የሚደርስብን ነገር የለም" ሲል ሊያጽናናት ሞከረ:: ወዲያውም በሽሪጡ እንዳለ ውቅያኖሱን ለማየት ወደ ውጭ ሮጠ:: እነሆ:- ለማመን የሚያስቸግር÷ ከአሥራ አምስት ክንድ በላይ ወደ ሰማይ ከፍ ያለ የውኃ ግድግዳ እነርሱ ወዳሉበት እያጓራ ሲጣደፍ ተመለከተ:: በዚህን ጊዜ ከሕፃናቱ አብዛኞቹ ሽብሩን ሰምተው ወደ ውጭ ወጥተዋል:: ወዲያውም ቀልጣፋው የእግዚአብሔር ሰው÷የመጣውን አደጋ ስላስተዋለ÷ለመሸሽ ወሰነ:: የሚቻለውንም ያክል ጮክ ብሎ÷ሁሉም ወደ ጀልባው ፈጥነው እንዲገቡ አዘዘ:: አንድ አሮጌ አነስተኛ ጀልባ ነበራቸው::

ሕፃናቱን÷ ረዳቶቹንና የራሱን ቤተሰብ በዚያች አነስተኛ አሮጌ ጀልባ ውስጥ በዕምነት አጎረ:: ከዚያም ከረዳቶቹ አንዱ የጀልባውን ሞተር ሲቀሰቅስ ያለወትሮው በቅጽበት ተነሣላቸው:: ሳንደርስ በኋላ እንደ መሰከረው÷ ያ ጀልባ ከዚያ በፊት አንድም ቀን÷በአንዴ ተነሥቶ አያውቅም ነበር:: ስለዚህ ይህም እንኳ ራሱን የቻለ ተዓምር ነበር:: በዚህ አኳኋን ከሞገደኛው ሞገድ ቁጣ ፊት ዞር ማለት ጀመሩ::

ከዚያም ሕፃናቱንና ቤተሰቡን በጀልባው አጭቆ÷ ከሚያጓራው የባሕር ክምር ፊት ትንሽ አልፍ እንዳሉ÷ ማዕበሉ መዋዕለ ሕፃናቱን ሲፈነቃቅል ተመለከቱ:: ወንድማችን ሳንደርስ ነገሩ ካለፈ በኋላ ሲያስታውስ:- "የነጎድጓድ ድምፅና ጨለማ መሳይ ባሕር ነበር":: ወዲያውም "ማዕበሉ ጋራዣችንን ሲፈነቅለውና÷ አዲስ ቶዮታ የጭነት መኪናችን ከጋራዥ ውስጥ ተተፍቶ ሲወረወር ተመለከትሁ":- ብሏል::

## ማምለጫ

ከዚህ በታሪክ ውስጥ ወደር ካልተገኘለት የባሕር ቁጣ ለማምለጥ በእግዚአብሔር ታምኖ የወጣ ይህ አማኝ ሰው የቤቱን መፈራረስ እየተመለከተ በሞገድ ፊት ጀልባውን መቅዘፉ ቀጠለ:: በባሕሩ ላይና ውስጥ የተፈጠረው ነውጥ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ÷ጀልባቸው እንዳይገለበጥ ያሰጋ ነበር:: እነርሱ ከተነሡበት ሁለት ተኩል ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ድረስ አስፈሪ ሁኔታ ነበር:: በዚያን ወቅት ነበር የጌታ ቃል ከትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ወንድማችን ሳንደርስን ትዝ ያለው:: ወዲያውም የጌታ መንፈስ አበረታውና እጁን አንሥቶ ባሕሩን:- <u>"በጌታ በእየሱስ ስም አዝዞሃለሁ÷ጸጥ በል!"</u> ሲል ጮክ ብሎ በሥልጣን ገሰጸ:: ሳንደርስ:- <u>"ወዲያውም ባሕሩ ባለበት ጸጥ አለ:: እኔም በዚያን ጊዜ የባሕሩ መታዘዝ ቅዠቴ መሰለኝ"</u> ሲል ለጋዜጠኞች በሰጠው ምስክርነት ገልጾአል::

በመጨረሻም ያ ሁሉ ነፍስ ከመጣባቸው መዓት አምልጠው ባቲካሎዋ በተባለች ከተማ በአንዲት አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጠለያ አገኙ ፤ እግዚአብሔር ይመስገን:: አዎን ወገኖች:- እየሱስ ክርስቶስ ትላንትናም ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው:: ብርና ወርቅ የለኝም÷ ያለኝን እሰጠሃለሁ÷ በናዝሬቱ በእየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ ያሉትን እናስታውስ:: የጌታ እየሱስ ክርስቶስ ስም ዛሬም ድንቅን ይሠራል፤ ክብር ለስሙ ይሁን:: ማንኛውንም ማዕበላችንን በዚህ ሕያው ስምና ሥልጣን ማዘዝ ተሰጥቶናል ፤ እግዚአብሔር ይመስገን:: እኛም እነዚህን ሕፃናት ለታደገው የእየሱስ ክርስቶስ ስም ሰግደን እናከብረዋለን:: እየሱስ ጌታ ነው::

(ይንን ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ÷ ከዋሽንግተን የላከልንን የጌታ ባሪያ ዘማሪ አሰፋ አብዲሣንና ቤተ ሰቡን ጌታ እየሱስ አብዝቶ ይባርክልን:: ጸጋው ይብዛላችሁ::

(ዋሽንግተን ፖስት ዲሰምበር 30 2004 ከዘገበው በተቻለ መጠን ተተረጎመ:: ሥዕል ከዋሽ/ፖስት አይደለም)